## ሊጦን ዘነግህ ዘ፯ ዕለታት
## ዘተናገሮ ቅዱስ ባስልዮስ ።

### ዘሰኑይ

ይ· ካ· ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ
ይእኀዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ
፪ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ
ነአኵቶ እስመ ዕቀበነ በኵሉ ሌሊት
ወአብጽሐነ እምጽልመት ውስተ
፫ ብርሃን እሙስና ውስተ ዘኢይማስን
፬ ፭ እምኢያእምሮ ውስተ አእምሮ
አማን ከመ ኑኀ ዕለትኒ በኵሉ ሰላም
ወጥዒና ይረስየነ ነሀሉ ወይኅፅር ሕዝቦ
፮ በኃይለ መላእክቲሁ ዘለኵሉ ግብረ
በረከት ሥልጣን ቦቱ እግዚአብሔር
አምላክነ ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ።

## የሰባቱ ዕለታት የነግህ ሊጦን ።
## ቅዱስ ባስልዮስ የተናገረው ።

### የሰኞ

ይ· ካ· ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ዳግመኛ እንማልዳለን ።

ስናመሰግነው ሌሊቱን ሁሉ ጠብቆ ከጨለማ ወደ ብርሃን አድርሶናልና ከጥፋት ወደ ሕይወት ካለማወቅ ወደ ፍጹም ዕውቀት አደረሰን ቀኑን ሁሉ በፍጹም ሰላም በሕይወት እንድንኖር ያደርገን ዘንድ በመላእክትም ኃይል ሕዝቡን ይጠብቃቸው ዘንድ ለበረከት ሥራ ሁሉ ሥልጣን ያለው ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ነው ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ።

www.ethiopianorthodox.org

ይ· ካ· እግዚእ ዘኵሎ ትእኅዝ አንተ
ኑኅ ዕለትኒ በኵሉ ሰላም ወጥዒና
ረሲየነ ነሀሉ እስመ አንተ ዓቀብከነ
በኑኅ ሌሊት አንተ እግዚእ ዘኵሎ
፪ ትእኅዝ መልአከከ ኄረ መራሔ ፈኑ
ለነ ወተሣሃለነ በከመ ዕበየ ሣህልከ
ወበከመ ብዝኅ ምሕረትከ ደምስስ
፪ አበሳነ ወኢአሐደ እምኔነ ውጹአ
ወግኑሠ ኢትረሲ እሞገስከ በእንተ
ዐቢይ ስምከ ዘተሰምየ በላዕሌነ
ሠራዬ ኩን ለነ ወኢትኅድገነ ሀበነ
ንርከብ ሞገሰ በቅድሜከ ወበቅድመ
፪ ክርስቶስ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ
ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት
ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ
ዓለም ። ይ· ሕ· አሜን ።

ይ· ካ· ሁሉን የምትይዝ ጌታ ሆይ ቀኑንም ሁሉ በፍጹም ሰላም በሕይወት እንድንኖር አድርገን ። አንተ ሌሊቱን ሁሉ ጠብቀኸናልና ። አቤቱ ሁሉን የምትይዝ አንተ የሚመራቸው ርኅሩኅ መልአክህን ስደድልን ። እንደ ቸርነትህ ብዛት ይቅር በለን ። እንደ ይቅርታህም ብዛት በደላችንን አጥፋልን ። ከእኛ ወገን አንዱንም ከባለሟልነትህ የወጣ የተለየም አታድርገው ። ደገኛ ስምህ በኛ ላይ ስለ ተጠራ ይቅር ባይ ሁንልን አትተወን ባንተ ፊትና በልጅህ በክርስቶስ ፊት ባለሟልነትን እንድናገኝ አድርገን ።

በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ።

ይ· ሕ· አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

## ዘሠሉስ ።

፪ ፪ ይ· ካ· ስምከ ሕያው ዘኢይመ
፪ ውት ትጉህ ዘኢይዴቅስ ፈጣሪ
ዘኢይደክም እግዚእ ሥሉጥ ላዕለ
ኵሉ አምላክ ዘኢይትኀባእ ። ዘኪያከ
ያንቀዕዱ ኵሉ ዘበሰማይ ወዘበምድር
፪ ዘፈጠርከ ለስምከ ይሰብሑ ወያእኵቱ
አንተ አኃዜ ዓለም እግዚአብሔር
አምላክነ ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ።

ይ· ካ· አምላክነ አምላከ ትፍሥሕት
ወአምላከ ኀሤት ተወከፍ ጸሎቶሙ
፪ ፪ ለአግብርቲከ ወለአእማቲከ እለ
ቆሙ ወመጽኡ ቤተ መቅደስከ ኀበ
የኀድር ኃይለ ስብሐቲከ ። ከመ
ይስአሉ ዘእምኀቤከ ርቅየተ
ወሕይወተ ኀድግ ሎሙ አበሳሆሙ

## የማክሰኞ ።

ይ· ካ· ስምህ የማይሞት ሕያው ነው
የማያንቀላፋ ትጉህ የማይደክም
ፈጣሪ ከሁሉ በላይ የሠለጠነ ጌታ
የማይሠወር አምላክ ።
ለስምህ ምስጋናን ያቀርቡ ዘንድ
የፈጠርሃቸው በሰማይና በምርድ ያለ
ሁሉ ወደ አንተ ያንጋጥጣል ዓለምን
የምትይዝ አንተ እግዚአብሔር
አምላካችን ነህ ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ።

ይ· ካ· የደስታ አምላክ አምላካችን
የኀሤትም አምላክ አንተ ነህ የምስጋ
ናህ ኃይል ወደሚያድርበት ወደ ቤተ
መቅደስህ መጥተው የሚደክሙ የወን
ዶችንም የሴቶችን ባሮችህን ልመ
ናቸውን ተቀበላቸው ። ከአንተ ዘንድ
የሚገኝ ጥምቀትን ሕይወትንም ይለ
ምኑ ዘንድ ። በደላቸውን ይቅር

www.ethiopianorthodox.org

ወኢትንጽር ምግባረ ኃጢአቶሙ
ወተወከፍ ንስሓሆሙ ይባእ ጸሎቶሙ
በቅድሜከ ከመ መአዛ ሠናይ ።
፪ እወ እግዚኦ አምላክነ ትሬኢ
ወኢታስተርኢ መሐሪ ነጽር ወተመ
የጠነ ከመ በዝነ ዓለም ወበዘይመ
ጽእ ንስግድ ወናልዕል ናእኵት ወንሰ
፪ ብሕ ስመከ ኄሩ በክርስቶስ ።
፫ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ
መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ
ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ይ· ሕ·
አሜን ።

ዓራራይ

## ዘረቡዕ ።

ይ· ካ· ለትሩጽ እግዚኦ ምሕረትከ
በላዕሌነ ወብርሃነ ገጽከ ላዕለ ነፍስነ
ይምጻእ ምሕረትከ ዘያሐይወነ ያስተ
ርኢ ኂሩትከ ዘያስተፌሥሐነ ዕቀበነ

በላቸው ። የኃጢአታቸውንም ሥራ
አታስብ ። ንስሓቸውን ተቀበላቸው ።
እንደ በጎ መዓዛም ልመናቸውን በፊ
ትህ ተቀበላቸው ። አቤቱ አምላካችን
ታያለህ አትታይም ። አቤቱ መሐሪ
ሆይ ተመልከተን ። ተመለስልንም
በዚህም ዓለም በሚመጣውም እንሰግ
ድልህ ዘንድ ክቡር ስምህንም ከፍ
ከፍ እናደርግ ዘንድ ፈጽመንም
እናመሰግን ዘንድ ። በርሱ ያለ ክብር
ጽንዕ ለአንተ ይገባል ከርሱ ጋራ
ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም
ዘወትርም ለዘላለሙ ።
ይ· ሕ· አሜን።

## የረቡዕ ።

ይ· ካ· አቤቱ ምሕረትህ ፈጥና
በላያችን ትደረግ ። የፊትህም ብርሃን
በሰውነታችን ላይ ። የሚያድነን
ምሕረትህ ይምጣ ደስ የሚያሰኘን

www.ethiopianorthodox.org

እግዚኦ እምኵሉ እኩይ ወእምኵሉ ስሕተት ወተወከፈነ በከመ ነቢብከ ። ግበር ሰላመ ማእከሌነ ወማእከሌከ እስመ ለዘኒ ስሕተ አንተ ትክል መይጠቶ መንገሌከ ። ወንሰግድ ለከ ውስተ አዕፃዳቲከ ዘኢይትኄለቍ ። እስመ አመ ዕለተ ጸራሕነ ኀቤከ አንተ ትሰምዐነ ። ወትፀውር ለነ ድካመነ ወትትዔገሠነ ኃጢአተነ ። እስመ መሐሪ አንተ እግዚአብሔር አምላክነ ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ።

ይ· ካ· እስመ አንተ ከመ ወልደ አብ ኄር ዘአስተርአይከ ውስተ ዓለም ከመ ትስቂ ወትኅፅነ እጓለ እመሕያውከ ወሊተኒ ለገብርከ ጸግወኒ ወትረ ብዕለ

ቸርነትህ ይገለጽ ። አቤቱ ከክፉ ነገር ከስሕተትም ሁሉ ጠብቀን እንደተናገርከውም ተቀበለን ። በእኛና በአንተ መካከል ሰላምን አድርግ የበደለውን ወደ አንተ መመለስ ይቻልሃልና ። ቍጥር በሌለው በቦታህ ሁሉ እንሰግድልሃለን ወደ አንተ በጮህን ጊዜ አንተ ትሰማናለህና ድካማችንንም ትሸከምልናለህ ኃጢአታችንንም ትታገሠናለህ አቤቱ አምላካችን እግዚአብሔር አንተ መሐሪ ነህና ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ይጸልዩ ።

ይ· ካ· መቼም መች ቸር የአብ የባሕርይ ልጅ አንተ ነህና ። የሰውን ልጅ ታሳድግ ዘንድ በዚህ ዓለም የተገለጽህ ። ለኔም ለባርያህ በጎ

ሠናያቲከ ። እስመ አንተ ትሁብ ሠናያተ ለኀሩያኒከ ወትጼጉ መድኃኒተ ለሕዝብከ ። ወፈቂደከ ታስተርኢ አስተርአይከ ። ወመኑ አምላክ መሐሪ ወቅዱስ ዘከማከ ። ወተሣሃለነ በከመ ዕበየ ሣህልከ ወበከመ ብዝኀ ምሕረትከ ደምሰስ አበሳነ በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም

ይ· ሕ· አሜን ።

## ዘሐሙስ ።

ይ·ካ· ከመ ታድኅነነ እግዚኦ እምዕለት እኪት ወእምሰዓታተ መንሱት ወእምኵሎሙ ዘእኩያን ትምይንት እምኀየት ወእምጽርዓት እምድድቅ ወእመጻኢት ። አድኅነነ እግዚኦ አምላክነ በዛቲ ሰዓት ። አኃዜ ዓለም እግዚአብሔር አምላክነ ።

ነገርን ስጠኝ ለመረጥካቸው በጎ ነገርን ትሰጣቸዋለህና ። ለወገኖችህም ደኅንነትን ትሰጣለህ ወደህ ተገለጽህ እንደ አንተ መሐሪ ቅዱስ አምላክ ማነው ። አሁንም እንደ ይቅርታህ ብዛት መጠን ይቅር በለን ። እንደ ቸርነትህም ብዛት በደላችንን ይቅር በለን ። በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ዕንዕ ለአንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ ።

ይ· ሕ· አሜን ።

## የሐሙስ ።

ይ· ካ· አቤቱ ከክፉ ቀን መከራ ከጥፋትም ሰዓቶች ታድነን ዘንድ ከክፉ ሰዎችም ተንኰል ከሀኬት ከጽርዓት ድንገት ከሚመጣ (መከራ) አቤቱ አምላካችን በዚህች ሰዓት አድነን ዓለምን የያዝህ አምላካችን እግዚአብሔር አንተ ነህ ።

www.ethiopianorthodox.org

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ።

ይ· ካ· እወ እግዚኦ አምላክነ እስመ
፲ ዘእምኀቤከ ውእቱ ረድኤት ወድኅ
ነት ወኵሎሙ እለ ይትማኅፀኑ ኀበ
ዘዚአከ መለኮት ። ዘአንተ አድኀንኮ
ለዳዊት ገብርከ እምኲናተ እኪት ።
ወለዳንኤል እምአፈ አናብስት ።
፲፩ ወለሶስና እምእደ ረበናት ለአናንያ
፲፪ ወአዛርያ ወሚሳኤል እምእቶነ እሳት
ዘይነድድ ። አድኅነነ እግዚኦ አምላ
ክነ እምትውልድ ዕሉት ወግፍትዕት
ወተማኅፀነ ነፍስነ ወሥጋነ በዘዚአከ
ኂሩት ።
፲፫ ፲ ወዕቀብ አብያተ ክርስቲያናቲከ በስ
ብሐት ወበጸሎት ወበርትዕት ሃይማኖት
ተሣሃለነ አምላክነ አቡነ ዘበሰማያት

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ይጸልዩ ።

ይ· ካ· እውነት ነው አቤቱ አምላካችን
ረድኤትና ድኅንነት የሚገኝ ከአንተ
ዘንድ ነውና ጌትነትህንም የተማፀኑ
ሁሉ ። ባርያህን ዳዊትን ከክፉ ጦር
ያዳንከው ። ዳንኤልንም ከአንበሳ አፍ
ሶስናን ከረበናት እጅ አናንያንና
አዛርያን ሚሳኤልንም ከባቢሎን
እሳት ያዳንካቸው። አቤቱ አምላካችን
እኛንም ከአሉተኛና ከዓመፀኛ ትው
ልድ አድነን ነፍሳችንንና ሥጋችንን
በቸርነትህ ጠብቅ ። ቤተ ክርስቲያና
ችንን በምስጋናና በጸሎት በቀናች
ሃይማኖትም ጠብቅ ። አምላካችን
ሆይ ይቅር በለን ። አባታችን ሆይ
በሰማይ የምትኖር ወደፊተና አታግ

www.ethiopianorthodox.org

ኢታብአነ ውስተ መንሱት አላ አድ
፬ ኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ እም
ተመውዖ ለሰይጣን እምሕርትምና
፬ ወእምድቀት ። ርድአነ ንትቀነይ ለከ
ዘእንበለ ድካም ወሀኬት ወትረ በኵሉ
፬ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ። በ፩ዱ ወልድከ
ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ
መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘ
ልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ይ፡ ሕ፡ አሚን።

## ዘዓርብ ።

፬ ይ፡ ካ፡ ተዘከር እግዚኦ ለለ፩ዱ ፩ዱ
ስእለቶ ተዘከር እግዚኦ ለለ፩ዱ ፩ዱ
እምከርሠ እሙ ። ተዘከር እግዚኦ
ብዙኃነ አሕዛበ እለ በርትዕት
ሃይማኖት የሐይዉ እንስቲያሆሙ
ዕቀብ ወራዙቶሙ ሠርሕ ርሱዓነ
አጽንዕ ቅጥቁጣነ ባልሕ ወዝርዋነ

ባን ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ ።
ለሰይጣን ከመሸነፍ ከመዋረድና
ከመውደቅ አድነን ። በየጊዜው
በየሰዓቱ ሁሉ ያለ ድካምና ያለ ሀኬት
እናገለግልህ ዘንድ እርዳን ።
በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ
ለአንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ
ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም
ለዘላለሙ ይ፡ ሕ፡ አሜን ።

## የዓርብ ።

ይ፡ ካ፡ አቤቱ የያንዳንዱን ልመናውን
አስብ አቤቱ እያንዳንዱን ከእናቱ
ማኅፀን ጀምረህ አስብ በቀናች
ሃይማኖት የሚኖሩትን ብዙ አሕዛብን
አስብ ሴቶቻቸውን ጠብቅ ጕል
ማሶቻቸውንም አቅናና ሽማግሎቻቸ
ውን አጽና የተቀጠቀጡትን አድን

www.ethiopianorthodox.org

አስተጋብእ ። ለእለ ይነግዱ ንግድ ምስሌሆሙ ወለእለ ይትመነደቡ አድኅኖሙ ። ወለእለ ውስተ ተስናን ወቅኔት መሪር ይሄልዉ አንተ አኃዜ ዓለም ተዘከር **እግዚአብሔር** አምላክነ ።

**ይ· ዲ·** ጸልዩ ።

**ይ· ሕ·** አቡነ ዘበሰማያት ።

፲፪ **ይ· ካ· እወ እግዚእ አምላክነ** ለመዓስብ ከዳኒ ወባላሒ ለእጓለ ማውታ ለዱያን ዐቃቤ ሥራይ ። ለእለ ይነግዱ መርሰ ወዛኀን እስመ አንተ **እግዚአብሔር** ተአምር ወትጤ

፲፫ ይቅ ለለ፩ዱ ፩ዱ ስእለቶ ወንብረቶ ወትካዘ ቤቱ ። **አድኅን እግዚእ** ዛተኒ ሀገረ ወካልአተኒ አህጉረ ወበሐውርተ ወእለ በሃይማኖተ ዚአከ የኀድሩ

የተበተኑትን ሰብስብ መንገድ ከሚሄዱት ጋራም ሂድ የሚጨነቁትን አድን በፀብ በፅኑ አገዛዝ የሚኖሩትንም ዓለምን የያዝህ አንተ አምላካችን **እግዚአብሔር ሆይ** አስባቸው ።

**ይ· ዲ·** ጸልዩ ።

**ይ· ሕ·** አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ ።

**ይ·ካ· እውነት ነው አቤቱ አምላካችን** ባልቴትዋን የምትረዳ አባት እናት የሌለውን ልጅ የምታድን ለታመሙት ባለመድኃኒት መንገድ ለሚሄዱት ወደብ ጸጥታ ነህ ። **አንተ የያንዳንዱን ልመናውንና** አኗዋሩን የቤቱንም አሳብ መርምረህ ታውቃለህ ትረዳለህና ። **አቤቱ** ይህች አገር ሌሎችም አገሮች በአንተ ሃይማኖት የሚኖሩባቸውን አውራጃዎችንም

www.ethiopianorthodox.org

ውስቴቶን። ቅዱሳነ አድኅን እምድል
፪ ቅልቅ ወእምረኃብ ወእመራደ ካልእ
ሕዝብ ። ሐዋዘ ብርሃነ ጸግወነ ወእእ
ትት ኑፋቄ እምቤተ ክርስቲያንከ ።
ወደምረነ ምስለ ደቂቀ ብርሃነ
ስብሐቲከ ሀበነ ከመ በ፩ዱ ልብ
ወበ፩ዱ አፍ ንሰብሕ ለአብ ወወልድ
ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ
ወለዓለመ ዓለም ይ፡ ሕ፡ አሜን ።

## ዘቀዳሚት ።

ይ፡ ካ፡ ቀዳሜ ጸጋ ኢየሱስ ክርስቶስ
፪ ኃይሉ ወጥበቡ ለአቡሁ እስመ አንተ
ውእቱ በግዑ ለእግዚአብሔር
ዘያአትት ኃጢአተ ዓለም ተሣሃለነ
እስመ ወረድከ እምሰማይ በመስፈርተ
ጥበቡ ለአቡከ ከመ ታድኅን ልሐ
ኰተከ ዘአንተ ለሐኰ መዋቲ

አድን ። ቅዱሳንን ከመናወጥና ከረኃብ
ከሌላም ወገን ከሚመጣባቸው
ወራሪ አድን ። ያማረ ብርሃን ስጠን ።
መጠራጠርንም ከቤተ ክርስቲያንህ
አርቅ የምስጋናህ ብርሃን ልጆች
ከሚሆኑት ጋራ አንድ አድርገን ።
አንድ ልብ አንድ ቃል ሆነን አብን
ወልድን መንፈስ ቅዱስንም
እናመሰግን ዘንድ ስጠን ። ዛሬም
ዘወትርም ለዘላለሙ ይ፡ ሕ፡ አሜን ።

## የቅዳሚት ።

ይ፡ ካ፡ የስጦታ መጀመሪያ ኢየሱስ
ክርስቶስ ለአባቱ ኃይሉ ጥበቡ ነው ።
የዓለምን ኃጢአት የምታርቅ የእግዚአ
ብሔር በግ አንተ ነህና ይቅር በለን ።
በአባትህ በጥበቡ መስፈርት ከሰማይ
ወርደሃልና ። አንተ የፈጠርከውን
ሟች ተለዋጭ የሆነ ፍጥረትህን

www.ethiopianorthodox.org

ዘይማስን ። ዘየሐውር በክንፈ ነፋስ ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈሰ ወለእለ ይትለአክዎ ነደ እሳት ። ዘይኔጽራ ለምድር ወይሬስያ ከመ

፪ ትርዐድ ዘይገሥሦሙ ለአድባር ወይጠይሱ በመንፈሰ ጸጋከ አጽን ያሙ ለሕዝብከ አንተ አኃዜ ዓለም **እግዚአብሔር** አምላክነ ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ።

፪ **ይ· ካ· እወ እግዚእ አምላክነ በመን ፈሰ ጸጋከ** አስተፍሥሐሙ ለሕዝ ብከ ። እስመ አንተ ውእቱ መቅለሊ ዕፁብ ረዳኤ ምንዱብ ሠረጎሙ **ለሐዋርያት** ንዋዮሙ ለነዳያን ተስ ፋሆሙ ለቅቡፃን መንሥኢሆሙ

፪ ለሙታን **ኢየሱስ ክርስቶስ** ኃይሉ ወጥበቡ ለአቡሁ ። ኪያከ ነአኵት ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ።

ይ· ሕ· አሜን ።

ታድን ዘንድ በነፋስ ክንፍ የሚሄዱ መላእክትን ረቂቃን የሚያገለግሉት ንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋ ቸው ። ምድርን አይቶ እንድትንቀጠ ቀጥ ያደርጋታል ተራራዎችንም ይዳስ ሳቸዋል ይጨሳሉ ። ዓለምን የያዝህ አንተ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ በስጦታህ መንፈስ ወገኖችህን አጽናቸው ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ።

**ይ· ካ· እውነት ነው አቤቱ አምላካችን ሆይ** በስጦታህ መንፈስ ወገኖችህን ደስ አሰኛቸው ። ጭንቁን ነገር የምታቀል የተቸገረውን የምትረዳ አንተ ነህ ። **የሐዋርያት** ጌጣቸው የነዳያን ገንዘባቸው ተስፋ ላጡ ሰዎች ተስፋቸው ሙታንንም የምታነሣቸው **ኢየሱስ ክርስቶስ** ሆይ ለአብ ኃይሉ ጥበቡ የምትሆን አንተን እናመሰግና ለን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ ።

ይ· ሕ· አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

## ዘቀዳም ሥዑር ።

ይ· ካ· ሶበ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ ይብል እስራኤል ሶበ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ ። እንተ ጊዜ ተንሥአ ሰብእ ላዕሌነ አሐዝብ ሕያዋኒነ እምውኅጡነ በከመ አንሥኡ ቊጥዐ መዓቶሙ ላዕሌነ ። አሐዝብ በማይ እምአስጠሙነ ። እምውኂዝ አምሰጠት ነፍስነ አምሰጠት ነፍስነ እማየ ሀከክ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክነ ዘኢያግብአነ ውስተ መሥገርተ ማዕገቶሙ ። ነፍስነሰ አምሠጠት ከመ ዖፍ እመሥገርት ነዓዊት ። መሥገርትሰ ተቀጥቀጠት ወንሕነሰ ድኅነ ። ረድኤትነሰ በስመ እግዚአብሔር አምላክነ ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ።

## የቅዳሜ ሥዑር ።

ይ· ካ· እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ባይኖር ይላል እስራኤል ። እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ባይኖር ሰው በላያችን በተነሣ ጊዜ በሕይወታችን በዋጡን ነበር ። ቊጣቸውን በላያችን እንዳነሡ በውኃ ባሰጠሙን ይመስለኛል ። ነፍሳችን ከፈሳሽ አመለጠች ። ነፍሳችን ከክርክር ውኃ አመለጠች በሚከብ ወጥመዳቸው ውስጥ ያላገባን እግዚአብሔር ይመስገን ። ነፍሳችን ግን እንደ ዖፍ ከአዳኝ ወጥመድ አመለጠች ። ወጥመድ ተሰበረች እኛም አመለጥን ። ረድኤታችን ግን ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር ስም ነው ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ።

www.ethiopianorthodox.org

ይ· ካ· ዘገብረ ሰማየ ወምድረ ።

ዘገብረ ሰማየ ወምድረ

ዘገብረ ሰማየ ወምድረ ለዓለም

ወለዓለመ ዓለም ይ· ሕ· አሜን ።

## ዘእሁድ ።

፩ ይ· ካ· ወካዕበ ናስተበቍዖ ለአምላከ
ምሕረት ዘረዳእኮ ለአብርሃም አመ
ይቀትሎሙ ለነገሥት ዘአድኀንኮ
ለይስሐቅ እምነ መጥባሕት ዘመራ
ሕኮ ለያዕቆብ በውስተ መንገድ
፪ ወአስተርአይኮ በራእየ ሌሊት በኀበ
አቀሞን ለሐውልት ዘአዕበይኮ
ለዮሴፍ በብሔረ ባዕድ እግዚአብሔር
አምላክነ ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ።

፫ ይ· ካ· እወ እግዚእ አምላክነ ዘኀደ
ፍኮ ለኖኅ በውስተ ታቦት ወለዳንኤል

ይ· ካ· ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ።

ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ።

ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ። ለዘላ
ለሙ ይ· ሕ· አሜን ።

## የእሑድ ።

ይ· ካ· የምሕረት አምላክን ዳግመኛ
እንማልደዋለን ። ነገሥታቱን በወጋ
ቸው ጊዜ አብርሃምን ያዳንከው ይስሐ
ቅን ከመጥባሕት ያዳንከው ያዕቆብን
በመንገድ የመራኸው ድንጋዩን ባቆ
መበት ቦታ ሌሊት በራእይ የታየኸው
ዮሴፍን በባዕድ ሀገር ከፍ ከፍ ያደረግ
ኸው አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ።

ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ ።

ይ·ካ· እውነት ነው አቤቱ አምላካችን
ኖኅን በመርከብ ያሻገርከው አንተ

www.ethiopianorthodox.org

እም አፈ አናብስት ወለሶስና እምእደ
ረበናት ዘለአኮ ለሙሴ ምስለ ዐቢይ
ረድኤት ዘመራሕኮሙ ለሕዝብከ
መዓልተ በደመና ወኵሎ ሌሊተ
በብርሃነ እሳት ። ዘተናገርከ በዲበ
ነቢያት ። ወአስተርአይከ ጸጋከ ላዕለ
፱ ሐዋርያት እንዘ ጉቡኣን እሙንቱ
፲ ውስተ ፩ዱ ቤት ወረደ ላዕሌሆሙ
መንፈስ ቅዱስ ከመ ዘእሳት ወተናገሩ
በነገረ ኵሉ በሐውርት ውእተ
መንፈሰከ ፈኑ ዓማዴ ሰማይ ወምድር
ባርክ ማኅበረነ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ
ሰዓት ። በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ
ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ
ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ
ወለዓለመ ዓለም ይ· ሕ· አሜን ።

ነህ ። ዳንኤልን ከአንበሳ አፍ ያዳን
ከው ። ሶስናን ከረበናት እጅ ያዳን
ካት ። ሙሴን ከታላቅ ረድኤት ጋራ
የላክኸው። ወገኖችህንም ቀን በደመና
ሌሊቱን ሁሉ በእሳት ብርሃን የመራ
ኻቸው በነቢያት የተናገርህ በሐዋር
ያት ላይ ጸጋህን የገለጽህ አንተ ነህ ።
በአንድ ቤት ውስጥ ተሰብስበው ሳሉ
መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት ሆኖ
በላያቸው ወረደ ። በሀገሩ ሁሉ ቋንቋ
ተናገሩ ። ሰማይንና ምድርን የፈጠርህ
አንተ ይህንን መንፈስህን ላክልን ።
በየጊዜው በየሰዓቱ ሁሉ አንድነታች
ንን ባርክልን ። በአንድ ልጅህ በርሱ
ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል
ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ
ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ ይ· ሕ·
አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org